

አቡነ ጎርጎርዮስ ት/ቤቶች

የ **2012** ዓ.ም የትምህርት ዘመን የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ለሰባተኛ ክፍል የቀረበ የአማርኛ ቋንቋ የመለማመጃ ጥያቄ **(20%)**

ስም _____ ክፍል ___ ቁጥር ___

<u>መመርያ አንድ፡ ከተራ ቁጥር **1-5** ለቀረቡት ጥያቄዎች በአጠያየቃቸው መሰረት ትክክል የሆነውን “እውነት” ስህተት የሆነውን “ህሰት” በማለት መልሱ።</u>

1. ግጥም የሰውን ልጅ ቀንጥጦ የመያዝ ኃይል አለው።
2. ቃላዊ ግጥሞች ራሱን የቻለ እና የታወቀ ደራሲ አላቸው።
3. በህትመት መፀሃፍ ላይ ሰፍረው የሚገኙ ግጥሞችን የተፃፉ ግጥሞች እንላቸዋለን።
4. “የልጆች ጫወታ ግጥም” ከቃላዊ ግጥም ላይመደብ ይችላል።
5. ሚያዝያ ግብ ሲል ግንቦት ሲያገሳ
   አከናናቢ ጎድጓዳ ማሳ
   የሚለው ግጥም የሥራ ግጥም ነው፤ ሊባል ይችላል።

መመርያ ሁለት፡ በ “ህ” ስር ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከ “ለ” ስር በመፈለግ አዛምዱ።

“ህ”	“ለ”
6. መደንቀር	ሀ. ዶም ፀሎት
7. ምህላ	ለ. መስጠት
8. አበሳ	ሐ. ማዳን
9. መቸር	መ. ደግ
10. መታደግ	ሠ. መገተር
	ረ. መከራ
	ሰ. መቸገር

መመርያ ሦስት፡ ከተራ ቁጥር **11-15** ለቀረቡት ጥያቄዎች በአጠያየቃቸው መሰረት ትክክለኛውን ምላሽ በመምረጥ መልሱ።

11. ትልቋ እህታችን _____ መጣች። ባዶ ቦታውን ማሟላት ያለበት ትክክለኛ ቃል ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?
    ሀ. ነገ ለ. ማታ ሐ. ወጪ መ. ዘወትር
12. የሌላን ሰው ሃሳብ ቀድቶ ለመጠቀም የሚያገለግል የሥርዓተ ነጥብ ዓይነት ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?
    ሀ. ነጠላ ሰረዝ ለ. ድርብ ሰረዝ
    ሐ. ድርብ ትዕምርተ ጥቅስ መ. ትምዕርተ አንክሮ
13. “ቅዱስ እቤት አለ።” የሚለው አረፍተ ነገር ምን አይነት ዓ.ነገር ነው?
    ሀ. ጥያቄያዊ ነው። ሐ. አሉታዊ ነው።
    ለ. ትዕዛዛዊ ነው። መ. አዎንታዊ ነው።
14. የዚህ ግጥም ደራሲ _____ ነው? ባዶ ቦታውን ማሟላት ያለበት ትክክለኛ መጠይቃዊ ቃል የቱ ነው?
    ሀ. ማን ለ. ምን ሐ. ለምን መ. መቼ
15. ከጠፍር ወይም ከገመድ የሚሰራ የድንጋይ መወርወርያ መጠርያ የሆነው የቱ ነው?
    ሀ. ሰርዶ ለ. አልቢን ሐ. አውድማ መ. ወንጭፍ

መመርያ አራት፡ ከሥር በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ የሚታዩትን ተውሳከ ግሶች በደንብ በማንበብ የጊዜ ተውሳከ ግስ፣ የቦታ ተውሳከ ግስ፣ የሁኔታ ተውሳከ ግስ ወይም የመጠን ተውሳከ ግስ በማለት ለይታችሁ ፃፉ።

16. አልማዝ ትምህርት ቤት ነች።_____
17. አስቴር ነገ ትመጣለች።_____
18. አስካለ ቶሎ መጣች።_____
19. ኳሷ በጣም ትንሽ ናት።_____
20. ሔኖክ እዚህ ነበር።_____